# እንነጋገር…

## ለውጥ ያመጣል!



| መቼ | ርዕስ |
|---|---|
| **ልጅዎን በሚያልብሱበት ወቅት…** | ልጅዎ ስለሚለብሳቸው ልብስ፣ ካልሲና ጫማ ተነጋገሩ። ዛሬ ስለሚከሰት ወይም ትላንት ስለተከሰተ ነገር ተጫወቱ። |
| **ምግብ በሚያበስሉበት ወቅት…** | ለልጅዎ መለኪያ ማንኪያዎች፣ የፕላስቲክ ጎድጓዳ ሰሃኖችና ድስቶች ይስጧት፤ በእነዚህ ነገሮች ምን እንደምታደርግ እንድትነግርዎት ዕድል ስጧት። ስለምታደርጉት ነገር ተነጋገሩ። |
| **ምግብ በሚበላበት ጊዜ…** | ይህንን ጊዜ በመነጋገር ተዝናኑበት። ዛሬ ያደረጋጅሁትን ተወያዩ። ልጅዎ ቀኑ እንዴት እንደነበር እንዲነግርዎት ያበረታቱት። ዛሬ የሰማችሁትን ታሪኮች ወይም ቀልዶች አካፍሉ። |
| **ገላ በሚታጠብበት ጊዜ…** | ውሃው እንዴት እንደሆነና ስለ ውሃ መጫዎቻዎቹ ተነጋገሩ። የሰውነቷን ልዩ ልዩ ክፍሎች ይለዩና ይንገሯት። ዘፈኖች ዝፈኑ ወይም ግጥሞችን ግጠሙ። |
| **በመኝታ ጊዜ…** | ታሪኮች ተናገሩ፡- ስለ ልጅነትዎ፣ ስለ ቤተሰብዎ፣ ስላደጉበት ቦታ። አብራችሁ ስላደረጋችኋቸው ነገሮች ትዝታ አውሩ። |
| **አንድ ቦታ በምትሄዱበት ጊዜ…** | እርስዎ የምታዩትን ነገር ይግለጹ፣ ልጅዎም የሚያየውን ነገር እንዲገልጽ ያድርጉ። “በአይኔ የሆነች ነገር አያለሁ? እሷ ምንድነች?” ዓይነት ጨዋታ ተጫወቱ። መኪናዎች ቁጠሩ። |
| **ልብስ ማጠቢያ ቤት…** | ልብሶች ምን ምን እንደሆኑ ለዩ። ልጅዎ አንዳንድ የሚያስፈልጉዎትን ነገሮች ማግኘት እንዲረዳዎት ይጠይቁት። ካልሲዎችን በጥንድ በጥንድ እንድታደርግ ጠይቋት። |

THE Agenda for Children

**The Agenda for Children**
119 Windsor Street, Cambridge, MA 02139
phone 617-665-3812 fax 617-665-3888

## ክንያቱም

| | |
|---|---|
| **ድምጽዎ ሕጻን ልጅዎን ያረጋጋል።** | ልጅዎ ልክ እንደተወለደ ጭንቅላቱን ድምጽዎ ወደሚመጣበት አቅጣጫ ያዞራል። |
| **ሕጻን ልጅዎ መናገር የምትማረው እንደዚህ ነው።** | ልጅዎ እርስዎ የሚያሰሙትን ድምጾች መልሳ ትደግማለች። እሷ የምታሰማቸውንም ድምጾች መልሰው በመድገም መዝናናት ይችላሉ! |
| **ከፍ ያለው ልጅዎ አዳዲስ ቃላት የሚማረው እንደዚህ ነው።** | ልጅዎ የሚሰማቸውን ቃላት ይደግማል። ብዙ ቃላት ማወቅ ምን እንደሚያስፈልገው ወይም ምን እንደሚፈልግ ለእርስዎ ለመግለጽ ያስችለዋል። |
| **መዋለ ሕጻናት ለመግባት የደረሰችው ልጅዎ ስለምትኖርበት ዓለም የምትማረው እንደዚህ ነው።** | ቃላቶች ነገሮችንና ሐሳቦችን ይገልጻሉ። ልጅዎ ብዙ ቃላት ባወቀ ቁጥር ይበልጥ ትረዳለች። |
| **መናገርና ማዳመጥ ልጅዎን ለማንበብና ለመጻፍ ያዘጋጃል።** | ልጅዎ ቃላቱን የሚያውቅና የሚረዳ ከሆነ ማንበብና መጻፍ ለመማር ይቀልለዋል። |



# እንነጋገር...

## ለውጥ ያመጣል!

© 2002 Agenda for Children